## በመቆጠብ የሚገኝ የዕጣ ቁጥር (ኩፖን) ብዛት

ደንበኞች ከሚቆጥቡት የገንዘብ መጠን አንጻር ቀጥሎ በሰንጠረዥ የቀረበውን ያህል ኩፖን ያገኛሉ።

| የቆጠቡት የገንዘብ መጠን (በብር) | የሚያገኙት ቲኬት /የዕጣ ቁጥር/ ብዛት |
|---|---|
| 500-1,000 | አንድ |
| 1001-1,500 | ሁለት |
| 1,501-2,000 | ሶስት |
| 2,001-2,500 | አራት |
| 2,501-3,000 | አምስት |
| 3,001-3,500 | ስድስት |
| 3,501-4,000 | ሰባት |
| 4,001-4,500 | ስምንት |
| 4,501-5,000 | ዘጠኝ |
| ከ 5,000 በላይ | አስር |

## ያስተውሉ!

- ✓ ተጨማሪ ገንዘብ ሲቆጥቡ የሚያገኙት ኩፖን ብዛት ይጨምራል።
- ✓ ማንኛውም ቆጣቢ ሊያገኝ የሚችለው ከፍተኛው የዕጣ ቁጥር ብዛት 10 ሲሆን፣ ይህም የሚወሰነው በሚቆጠበው ገንዘብ መጠን ነው።

## ደንበኞች ለተለያዩ የሽልማት ዕጣዎች ብቁ ተወዳዳሪ ሆነው የሚካተቱበት ሁኔታ

አንድ ደንበኛ የሽልማት መርሐ ግብሩ ከጀመረበት ቀን አንስቶ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ከቆጠበው የገንዘብ መጠን አንጻር ኩፖን አግኝቶ፡-

- ✓ ለአራት ወራት ብር 500 እና ከዚያ በላይ ሳያወጣ በሒሳቡ ለማቆየት ከቻለ፣ ለ1ኛ ደረጃ ዕጣ (ማለትም ለመኖሪያ አፓርትመንት ቤቶች) ብቁ ተወዳዳሪ ይሆናል፤
- ✓ ለሦስት ወራት ብር 500 እና በላይ ሳያወጣ በሒሳቡ ለማቆየት ከቻለ፣ ለ2ኛ ደረጃ ዕጣ (ማለትም ለአውቶሞቢል መኪናዎች) ብቁ ተወዳዳሪ ይሆናል፤
- ✓ ለሁለት ወራት ብር 500 እና በላይ ሳያወጣ በሒሳቡ ለማቆየት ከቻለ፣ ለ3ኛ ደረጃ ዕጣ (ማለትም ለባለ 3 እግር ተሽከርካሪዎች) ብቁ ተወዳዳሪ ይሆናል።
- ✓ ለአንድ ወር ብር 500 እና በላይ ሳያወጣ በሒሳቡ ለማቆየት ከቻለ፣ ለ4ኛ ደረጃ ዕጣ (ለላፕቶፖች) ተወዳዳሪ ይሆናል።
- ✓ ከቀረቡት የሽልማት ዓይነቶች ለአንዱ ደረጃ ብቁ የሆነ ደንበኛ ብቁ በሆነበት ዕጣ ሽልማት ካልደረሰው ቀጥሎ ላለው ዕጣ ለውድድር ብቁ ይሆናል። ለምሳሌ፣ ለ2ኛ ዕጣ ብቁ ሆኖ ሽልማት ያልደረሰው ደንበኛ ለ3ኛ ዕጣ ብቁ ይሆናል፤ በዚህ ዕጣ ሽልማት ካልደረሰው ለ4ኛ ዕጣ ብቁ ሆኖ እንደገና ይወዳደራል።

አንድ ደንበኛ በአንድ የሽልማት ፕሮግራም ከአንድ በላይ ሽልማት ሊያሸንፍ አይችልም።

## ዕጣ አወጣጥ

- ✓ የዕጣ አወጣጥ ሥነሥርዓት በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ኃላፊነት የሚመራ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ በብሄራዊ ሎተሪ አስተዳደር አዳራሽ ይወጣል።

## የሽልማት ማስተላለፍ ሥነ-ሥርዓት

ሽልማቶችን ለአሸናፊዎች የማስተላለፉ ሥነ-ሥርዓቱ እንደ አስፈላጊነቱ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም በዲስትሪክት ጽ/ቤቶች ይከናወናል።

**ቆጣቢዎች ይበረታታሉ!**
**መቆጠብ ያሸልማል!**


የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia
ጋምቢያ መንገድ ፓ.ሣ.ቁ፡- 255 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ 251-11-551-50-04
የደንበኞች ግንኙነት ማዕከል ያለ ክፍያ መጥሪያ፡- 951
የስዊፍት አድራሻ፡- CBETETAA
ኢ-ሜይል cbecommun@combanketh.com
cbecomu@combanketh.et
cbenoor-ifb@cbe.com.et
https://combanketh.et
www.facebook.com/combanketh
www.twitter.com/combankethiopia
www.linkedin.com/company/commercialbankofethiopia


# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
# Commercial Bank of Ethiopia

**1ኛ ዕጣ**
2 የመኖሪያ አፓርትመንቶች



**2ኛ ዕጣ**
10 ዘመናዊ አውቶሞቢሎች



**3ኛ ዕጣ**
30 ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪዎች



**4ኛ ዕጣ**
30 ዘመናዊ ላፕቶፖች



## እነሆ ከበርካታ አጓጊ ሽልማቶች ጋር

### 10ኛው ዙር "የይቆጥቡ፣ ይሸለሙ" መርሃ ግብር ተጀመረ!

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሽልማት የሚያስገኙ መርሐ ግብሮችን መስጠት ከጀመረባቸው ባለፉት 9 ዓመታት በርካታ ሽልማቶችን ለደንበኞች አበርክቷል። ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

| ተ.ቁ | የሽልማት ዓይነቶች | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ባለ 3 መኝታ የመኖሪያ ቪላዎች | 3 |
| 2 | ባለ 3 መኝታ አፓርትመንት ቤቶች | 13 |
| 3 | መለስተኛ የጭነት መኪናዎች፣ | 3 |
| 4 | ሚኒባሶች | 15 |
| 5 | አውቶሞቢሎች | 95 |
| 6 | ትራክተሮች | 45 |
| 7 | ባለ 3 እግር ተሽከርካሪዎች | 120 |
| 8 | ሞተር ሳይክሎች | 96 |
| 9 | የውሃ መሳቢያ ሞተሮች | 66 |
| 10 | የእህል ሞተር ወፍጮዎች | 6 |
| 11 | ጄኔሬተሮች | 15 |
| 12 | ላፕቶፖች | 137 |
| 13 | ፍሪጆች | 16 |
| 14 | ቴሌቪዥኖች | 59 |
| 15 | የልብስ ማጠቢያ ማሽኖች | 45 |
| 16 | ዘመናዊ ምድጃዎች | 60 |
| 17 | ታብሌቶች | 15 |
| 18 | ስማርት የሞባይል ቀፎዎች | 7,500 |

በ2013 ዓ.ም. የሚካሄደው የ10ኛው ዙር የ"ይቆጥቡ፣ ይሸለሙ" መርሐ ግብር በርካታና አጓጊ ሽልማቶችን ይዞ ቀርቧል።

ከሽልማቶቹ መካከልም በዋናነት የሚከተሉት ይገኙበታል።

| የሽልማት ደረጃ | የሽልማት ዓይነቶች | የሽልማት ብዛት |
|---|---|---|
| 1ኛ ዕጣ | ✓ ባለ 3 መኝታ ዘመናዊ አፓርትመንት ቤቶች | 2 |
| 2ኛ ዕጣ | ✓ ዘመናዊ አውቶሞቢሎች | 10 |
| 3ኛ ዕጣ | ✓ ባለ 3 እግር ተሽከርካሪዎች | 30 |
| 4ኛ ዕጣ | ✓ ዘመናዊ ላፕቶፖች | 30 |

## የ10ኛው ዙር "ይቆጥቡ ይሸለሙ" መርሐ ግብር የሚካሄድበት ጊዜ

የ10ኛው ዙር በሽልማት ላይ የተመረኮዘ መርሐ-ግብር "ይቆጥቡ፣ ይሸለሙ" በሚል ከታህሳስ 23 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ይከናወናል።

## ለሽልማቶቹ የመወዳደሪያ መስፈርት

- ✓ ለመርሐ ግብሩ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከባንካችን ቅርንጫፎች መካከል በአንዱ ከ500 ብር ያላነሰ መቆጠብ፤ እንዲሁም
- ✓ እስከ መርሐ ግብሩ ማጠናቀቂያ ጊዜ ድረስ የቆጠቡትን ገንዘብ አለማውጣት ይጠበቅባቸዋል።

## በሽልማት መርሃ ግብሩ የሚካተቱ የቁጠባ ሒሳብ አይነቶች

የሽልማት ዕጣ ውስጥ ለመሳተፍ የባንካችን ደንበኛ ሆነው ወይም አዲስ የቁጠባ ሒሳብ ከፍተው በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጨማሪ ገንዘብ መቆጠብ ይኖርብዎታል።

ሽልማቱ ውስጥ የሚካተቱ የቁጠባ ዓይነቶቹም መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ፣ የዳያስፖራ የቁጠባ ሂሳብ፣ የታዳጊ ወጣቶች የቁጠባ ሒሳብ፣የወጣቶች የቁጠባ ሒሳብ፣ የሴቶች የቁጠባ ሒሳብ፣ የበዓል የቁጠባ ሒሳብ ፣የሰርግ ቁጠባ ሒሳብ ፣ሙዳይ ቁጠባ ሒሳብ ፣የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሒሳብ፣ የለበይክ እና የዳያስፖራ የቤት ብድር የቁጠባ ሒሳብን ጨምሮ ሌሎች በዋዲያህ የተከፈቱ ሒሳቦች በሙሉ፣ በሙዳረባህ የተከፈቱ የኢንቨስትመንት ሒሳቦች በሙሉ ፣ እንዲሁም የትምህርት የቁጠባ ሒሳብ ናቸው።

ከግለሰብ ሒሳቦች በተጨማሪ የግል ኩባንያዎች፣ አክስዮን ማኅበራት፣ የህብረት ሥራ ማኅበራት እና ሌሎች ማህበራትም የዚህ ሽልማት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

## መርሐ ግብሩ የማይመለከታቸው የቁጠባ ሒሳብ አይነቶች

በመርሐ ግብሩ የማይካተቱ የቁጠባ ሒሳብ ዓይነቶች ተንቀሳቃሽ ሒሳቦች፣ የመንግሥት ሒሳቦች፣ የቤቶች ልማት ቁጠባ ሒሳብ (የኮንሲዩመር ብድር ሒሳብ)፣ የሌሎች ባንኮች ሒሳቦች፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሒሳቦች፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ሒሳቦች ናቸው።

## የሽልማት መወዳደሪያ ኩፖን አሰጣጥ

- ✓ ደንበኞች ከ500 ብር እና ከዚያ በላይ መጠን ያለው ገንዘብ ሲቆጥቡ ለተለያዩ ሽልማቶች ዕድለኛ የሚያደርጓቸውን የኩፖኖች (የዕጣ ቁጥሮች) ያገኛሉ።
- ✓ ኩፖኖች ለደንበኞች የሚሰራጩት ግልጽነት ባለው የኮምፒውተር መተግበሪያ ሥርዓት አማካኝነት ይሆናል።

## ኩፖኖችን ዋጋ ሊያሳጣ የሚችል ሁኔታ

ደንበኞች ከታህሳስ 23 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ባሉት ወራት ካስቀመጡት ገንዘብ ላይ ወጪ ቢያደርጉ በእጃቸው የገባ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ኩፖን ዋጋ ያጣል። ለምሳሌ አንድ ደንበኛ በባንክ ሒሳቡ ከብር 5,000 በላይ ገንዘብ ቆጥቦ 10 ኩፖኖች ያገኛል። ሆኖም በመርሐ ግብሩ ጊዜ ውስጥ ከዚያ ሒሳብ ላይ ብር 1,000 ወጪ ቢያደርግ ካገኛቸው ኩፖኖች ውስጥ 2ቱ ዋጋ ያጣሉ። ስለዚህም 8 ኩፖኖች ብቻ ይቀሩታል፡-